በወጉ ያላወቅነው የቢቸናው ብርቱ ደራሲ- አውግቸው ተረፈ

ፀሐፊ- ጌታ በለጠ ደበበ (ጎጃም፣ ደብረ ማርቆስ)

.....



የኢትዮጵያ ሥነ ፅሑፍ ታሪክ ሲነሳ ጎጃም በመጀመሪያው ረድፍ ላይ ይቀመጣል፡፡ ይህ የሆነው ጎጃም የብዙ የሥነ ፅሑፍ ጠብብት እና ሊቃውንት መፍለቂያ በመሆኑ ነው፡፡ አጅግ የበዙ የሥነ ፅሑፍ ሰዎች ከትላንት እስከ ዛሬ ከጎጃም ምድር ቢፈልቁም ታሪካቸው በወጉ ተመዝግቦ የሚገኘው የጥቂቶች ብቻ ነው፡፡ ለሐገር ታላቅ ውለታ ውለው ያለፉ ገድለ ብዙ ሰዎችን ትውልድ እንዲያውቃቸው ማድረግ የእኔ ዘመን ትውልድ ግዴታ ነው፡፡ የዚህ ፅሑፍ ዓላማ በኢየኢትዮጵያ ሥነ ፅሑፍ ታሪክ ውስጥ የራሳቸውን አሻራ ካስቀመጡ ታላላቅ የኪነ ጥበብ ሰዎች መካከል አንዱ ስለሆነው አውግቸው ተረፈ (ጎሩይ ሚናስ) ታሪክ በጨረፍታ ለአንባቢ ማስነበብ ነው፡፡

በጎጃም ክፍለ ሀገር በቢቸና አውራጃ ጨው ሰቅላ ማርያም ቀበሌ ውስጥ በ1942 ዓ/ም አንድ እንቁ እና ብርቱ ደራሲ ተወለደ፡፡ ስሙ ጎሩይ ሚናስ ተባለ፡፡ በልጅነቱ የቤተ ክህነት ትምህርት ጎጃም ውስት ባሉ ታዋቂ ቅኔ ቤቶች እየተዘዋወረ ተምሯል፡፡ጎሩይ ሚናስ አቡጌዳ፣ ቅኔ እስከ ዋዜማ እና ያመ ድጓን ከተማረ በኋላ በድቁና ተቀጥሮ ቤተ ክርስቲያንን አገልግሏል። የቅኔ እውቀቱን ለማሳደግ ጎጃም ውስጥ ዲማ ጊዮርጊስ ከአለቃ ማርቆስ ዘንዳ ተመዘገበ፡፡ ዲማ ጊዮርጊስ እልቆ ቢስ ሊቃውንትን በማፍራት፣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐይማት መዲና በመሆን ለረዥም ዓመታት ያገለገለ ቤተክርስቲያን ነው፡፡ ገዳሙ ከጥንት ከእነ አባ ተክለ አልፋ እሰክ የእነ አለቃ አያሌው ታምሩ ታላላቅ የቤተ ክህነት ሊቃውንት ጉባዔ ዘርግተው አስተምረውበታል፡፡ከአራቱ ጉባኤያት (ብሎያት፣

ሐዲሳት፣ መፅሐፍተ ሊቃውንት እና መፅሐፍተ መነኮሳት) በተጨማሪ ቅኔና ዜማ በወጉ ተነግሮበታል፡፡

ወደ ጉዳዬ ልመለስና ኀሩይ ሚናስ ልሳኑ የሚባል ጎንደሬ የቅኔ ቤት ባልንጀራ ነበረው፡፡ ልሳኑ ወደ ዲማ ጊዮርጊስ ከመምጣቱ በፊት አዲስ አበባን ያውቀው ነበር፡፡ በእንድ ወቅት ልሳኑ ኀሩይን አዲስ አበባ ቢኼዱ የተሸለ ትምህርት እንደሚማሩ እና በድቁና ስራ ተቀጥረው መስራት እንደሚችሉ ነገረው፡፡ ኀሩይ በሃሳቡ ተስማማ፡፡ ሁለቱ የቅኔ ተማሪዎች ደጀን ከተማ ድረስ በእግራቸው ከኼዱ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በእግር ለመኼድ አድካሚ ከመሆኑም በላይ ጊዜ የሚወስድ መሆኑን ተገንዝበው የትራስንፖርት ብር ለማግኘት ከደጀን ከተማ ዝቅ ብላ ከምትገኘው ቆላማ ሰፈር ከአርሶ አደሮች ቤት ስለንተ ማርያም አሉ፡፡ የማርያምን ሥም ጠርቶ መጠየቅ (መለመን አይባልም) የቤተ ክህነት ተማሪ ደንብ ነው፡፡ ሥርዓቱን ጥንቅቅ አድርጎ የሚያውቀው እና ለቤተክህነት ትምህርት ክብር ያለው የደጀን አርሶ አደር ለእነ ኀሩይ ጥጥ ሽጠው እንዲጠቀሙ ሰጧቸው፡፡

ከአርሶ አደሮች የተቀበሉትን ጥጥ በመሸጥ ለመኪና የትራንስፖርት የሚሆን ገንዘብ አገኙ፡፡ ለደላላ እና ለረዳት የሚከፈለውን ከፍለው በጭነት መኪና አዲስ አበባ ገቡ፡፡አዲስ አበባ ቀጨኔ መድኃኔዓለም አረፉ፡፡ በወቅቱ የቅኔ ተማሪዎችን ለማበረታታት አፈ ንጉስ ነሲቡ የተባሉ ግለሰብ ለተማሪዎች በወር ሦስት ብር እንዲከፈላቸው ያደርጉ ነበርና ኀሩይ ሚናስም በወር የሚከፈላቸውን ብር እየተቀበለ ኑሮውን በዚያው አደረገ፡፡

ኀሩይ ወር ጠብቆ የሚያገኛት ሦስት ብር በቁጠባ አሳደጋት፡፡ በርከት አለች፡፡ኀሩይ ያችን በጊዜ ሂደት የተጠራቀመች ገንዘብ ለአንድ ወዳጁ በአደራ ሰጠው፡፡ ሰውዬው የአደራ ግዴታውን አልተወጣም፡፡የኀሩይን ገንዘብ ይዞ ጎጃም ገባ፡፡ኀሩይ የዋዛ ሰው አይደለምና ተከትሎት ጎጃም ውስጥ ይስማ ደጀን ተብሎ የሚጠራ ቅኔ ቤት በመኼድ አቤቱታውን ለቅኔ ቤቱ መሪጌታ አቀረበ፡፡ ባለዕዳው መሐላ ፈፅሞ ከዳ፡፡ በዚህ ጊዜ ኀሩይ ከቤተሰቦቹ የትራንስፖርት ገንዘብ ተቀብሎ ተመልሶ አዲስ አበባ ኼደ፡፡

አሁን እንደ መጀመሪያው ቀጨኔ መድኃኔዓለም አልኼደም፡፡ወደ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን በመኼድ ኑሮውን ቢጀምርም ሕይወት ቀላል አልሆነችለትም፡፡ ከቅድሰት

ማርያም ቤተክርስቲያን ወጥቶ ብዙ የመከራ ሕይወትን ገፋ፡፡የአዲስ አበባ በረንዳ አዳሪዎችን ተቀላቀለ፡፡ የበረንዳ አዳሪነት ሕይወት ፈታኝ ነው፡፡ ጠኔው፣ እርዛቱ፣ ውሃ ጥሙን አልቻለውም፡፡

አንዳንድ ቀኖች ብሩህ ናቸው፣ የተስፋ ነፀብራቅ ይዘው ይዘው ይመጣሉ፡፡ በአንድ ወቅት ኅሩይ የብስራተ ወንጌል ራዲዮ ጣቢያ ሰባኪ ከነበሩት ከአለቃ ነብዬ ልዑል ጋር ተገናኘ፡፡ ኅሩይ ሚናስ በወር 12 የኢትዮጵያ ብር እየተከፈለው ለአለቃ ነብዬ ልዑል መፀሐፍ ቅዱስ በማንበብ፣ በመፃፍ እና መንገድ በመምራት በረዳትነት ተቀጠረ።በውላቸው መሰረት አለቃ ነብዬ ኅሩይን ዘመናዊ ትምህርት ሊያስተምሩት ነበር። ግን አልሆነም። በዚህ ጊዜ አውግቸው ከአለቃ ነብዬ ልዑል ጋር ያለውን ውል በማፍረስ የሐይማት መፅሔት፣ ውዳሴ ማርያም እና ጋዜጣ በማዞር ዘመናዊ ትምህርቱን ቀጠለ። በአስኳላው ትምህርትም ጎበዘ፡፡ በ1969 ዓ/ም አስራ ሁለተኛ ክፍል ተፈትኖ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚያስገባውን መቁረጫ ነጥብ አመጣ፡፡ በ1970 ዓ/ም ገናውን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተቀላቀለ፡፡ይሁንና ከዓመት በላይ መግፋትአልቻለም፡፡ ትምህርቱን እንዳይገፋ ያደረገው ፖለቲካ እንጅ የአቅም ውስንነት አልነበረም፡፡ ነገሩ ወዲህ ነው፡፡ኅሩይ በውቅቱ የኢህአፓ አባል ስለነበረ “ትምህርት ከድል በኋላ” በሚለው የኢህአፓ ታጋዮች መርህ መሰረት ትምህርቱን አቋርጦ ጀምሮት ወደ ነበረው የሕይወት መስመር ውስጥ ገባ፡፡ መፅሔት፣ የያሎት መፅሐፍት እና ጋዜጣ አዟሪነትን መተዳደሪያው አደረገ፡፡

የያሎት መፅሐፍት እና ጋዜጣ እያዞረ ሲሸጥ የነበረው ኅሩይ በጓደኞቹ ሃሳብ አምጭነት አንደ ቦታ ሆኖ ልብ ወለድ እና ሌሎች መፅሐፍትን መሸጥ ጀመረ፡፡ አሁን መደበኛ የመፀሐፍ ነጋዴ ሆኗል፡፡ የመፅሐፍ ንግዱ ሌላ የሕይወት መስመር አሳዬው፡፡ብዙ የሐገር ውስጥ እና የውጭ መፅሃፍትን አነበበ፡፡ታላቁን ደራሲ ስብሃት ገ/እግዚያብሔርንም የተዋወቀው በዚህ ወቅት ነበር፡፡ከደራሲ ስብሃት ጋር የጠበቀ ወዳጅነት መሰረቱ፡፡ መፅሐፍ ነጋዴ የነበረው ኅሩይ ሚናስ ደራሲ ሆነ፡፡ ወይ አዲስ አበባ የሚለውን መፅሐፍ አውግቸው ተረፈ በሚል የብዕር ሥም በየካቲት መፅሔት ላይ ወጥቶ ለንባብ በቃ፡፡ የትውልድ ሥሙን ትቶ ለምን በብዕር ሥም እንደፃፈ ሲጠየቅ “መፅሐፍ አዟሪ ስለነበርሁ ሰዎች ይተርቡኛል (በአራዳዎች አነጋገር ይፎግሩኛል ማለት ነው) ብዬ ነው” ሲል በሸገር ኤፍ

ኤም ከጋዜጠኛ መዓዛ ብሩ ሲያወጋ ሰምቸዋለሁ፡፡ በዚያም አለ በዚህ አሁን ጎሩይ ደራሲ ነው፡፡ ከእዚህ በኋላ ራሱ በመረጠው ሥም አውግቸው ተረፈ እያልሁ እቀጥላለሁ፡፡

“ወይ አዲስ አበባ” የተሰኘውን ድርሰት ካሳተመ በኋላ “አነወተቴ” እና ”እያስመዘከብኩ ነው” የሚሉትን ሁለት ድርሰቶች እንዲያትሙለት አታሚ ደርጅቶችን ቢጠይቃቸው ሁለቱም በዘመኑ የነበረውን የሳንሱርን ሕግ ማለፍ ባለመቻላቸው የህትመት ብርሃን ተነፈጉ፡፡በዚህም አውግቸው ተበሳጨ፡፡የአዕምሮ እክል የገጠመውም በዚህ መነሻነት ነው፡፡ድጋሜ መፀሐፍ መፃፍ እንደሌለበት ራሱን አሳመነ፡፡ ሙሉ ትኩረቱን መፅህፍ ንግድ እና ንባብ ላይ አደረገ፡፡ ደራሲ ስብሃትን ተዋውቆ ስለነበረ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፉ መፅሐፍትን እሳደደ ማነበቡን ተያያዘው፡፡ ከዓመት በኋላ ሌላ የዕድል ብርሃን ወደ አውግቸው ተረፈ መጣች፡፡ ከታላቁ ደራሲ እና ጋዜጠኛ ዳኛቸው ወርቁ ጋር ተገናኙ፡፡ ደራሲ እና ጋዜጠኛ ዳኛቸው ወርቁ በወቅቱ የኩራዝ አሳታሚ ድርጅት የቦርድ አባል ነበሩ፡፡ የአውግቸውን የስነ ፅሑፍ እውቀት የተረዱት ዳኛቸው ወርቁ አውግቸውን ኩራዝ ማተሚያ ድርጅት በመጽሐፍ አርታኢነት አስቀጠሩት፡፡ ለብዙ የድርሰት ሥራዎችም የአርትኦት ሥራ ሰራ፡፡ በዚህ ደርጅት ውስጥ እንዳለ “የአንገት ጌጡ” እና ሌሎችን የትርጉም ሥራችን ሰርቶ ለህትመት አበቃ፡፡ አሁን የተዋጣለት ደራሲ እና ተርጓሚ ሆኗል፡፡

ባሻዬ እስኪ ትቂት የደራሲውን ሥራዎች በመጠኑ እንቃኝ፡፡ ደራሲው ከሃያ በላይ ድርሰት እና የትርጉም ሥራችን ሰርቷል፡፡ ባይተዋር፣ ንፁህ ፍቅር፣ ደመኛው ሙሽራ፣ አንድ ሸ አንድ ተረቶች፣ የቀልዶች ማዕበል፣ ጣፋጭ የግሪም ተረቶች፣ ጨቤው፣ የፕሮፌሰሩ ልጆች ፣ የትውልድ እልቂት፣ የአማልዕክትና ጀግኖች ታሪክ፣ ስለሽና ስምንተኛው ሽህ፣ የግሪን ተረቶች፣ የህንድ ተረቶች፣ ቤቱ፣ የፍቅር ትንሳኤ፣ አስደናቂ የአለም ምርጥ ተረቶች ከአውግቸው ሥራዎች መካከል ናቸው፡፡ መከራና ችግርን ተጋፍጦ ይኼንን ሁሉ ሥራ መስራት የሚደንቅ ነው፡፡ ከአውግቸው ወጪ ማን ሊያደርገው ይችላል? ማንም፡፡

አውግቸው “እያስመዘገብኩ ነው” በሚለው ሥራው በደርግ ዘመን ሊነገር ቀርቶ ሊታሰብ የማያችለውን የዘመኑን አገዛዝ ነውረኝነት በድንቅ ቃላት አሸሞንሙኖ ኮንኗል፡፡ ሰውዬው ደፋር ነው፡፡ የአቢዮት ጠባዎችን ሕገ ወጥነት በሽጋ ብዕሩ ሞግቷል፡፡ የቀበሌ ሰራቶኞችን ፍሬ አልባ ስበሰባ ወዳጅነት እና ሕዝባዊ ወገንተንነት ማጣት አሳይቷል፡፡ በዘመን

የነበረውን መንግስታዊ ውስልትና፣ ጭቆና እና አድልዎ ‘ለምን’ ብሎ መጠየቅ እና ሁኔታውን ለመቀየር ብዕርን ይዞ መነሳት የአንድ ታላቅ ደራሲ መገለጫ ነው፡፡

“ወይ አዲስ አበባ” በሚለው የአጫጭር የልብ ወለዶች ስብስበ ሥራው ብዙ ማህበራዊ ኩነቶችን ነካክቷል፡፡ በተለይም ትኩረት ያለተሰጣቸው የከተማይቱ በረንዳ አዳሪ ዜጎችን ሕይወት ግልጥ አድርጎ አሳይቷል፡፡ በአንድ ወቅት ከበረንዳ አዳሪዎች መካከል አንዱ ሞቶ በመገኘቱ ወደ እስር ቤት የተወሰደው ገፀ ባህርይ እስር ቤቱን በእጅጉ ይወደዋል፡፡ ነገር ግን ታሳሪው የወንጀሉ አድራጊ መሆኑ በማስረጃ ባለመረጋገጡ ዳኛው ነጻ ብሎ አሰናበተው፡፡ ታሳሪው ከፋው፡፡ ያንን ውርጭ(ብርድ) እና ርሃብ ደጋሜ ለመጋፈጥ ማሰቡ ደከመው፡፡ ታሳሪው “ፖሊስ እንደ መልዕክ ሆኖ እስር ቤት ጨመረኝ፤ዳኛው ግን እንደ ሰይጣን ሆኖ ንፁህ ነው፤ ወንጀሉ ላይ የለበትም ብሎ አባረረኝ፡፡”ሲል የበረንዳ አዳሪዎች ህይወት ምንኛ የከፋ መሆኑን አሳይቷል፡፡

የአውግቸው ተረፈ ሌላው ሥራው “እብዱ”የተሰኘ ነው:: ይኼንን ድርሰት የጻፈው የአዕምሮ እክል ደርሶበት ከተሸለው በኋላ ነው፡፡ድርሰቱ በአዕምሮ ህመም የህክምና ባለሙያዎች ዘንድ ጠቃሚነቱ የጎላ ነው፡፡ድርሰጹ ብበዙ ተወዷል፡፡ አውግቸው ተረፈን “እብዱ”የተሰኘ ድርሰት ለማሰብ አማኑኤል ሆስፒታል ደራሲው ሲታከምበት የቆዬውን አንድ ህንፃ በሥሙ ሰይመውለታል፡፡ በህመም ውስጥ ሆኖ ሳይሰለቹ እና ሳይታክቱ የድርሰት ሥራ መስራቱ ልዩ ያደርገዋል፡፡ አውግቸው እውነትም ልዩ ነው፡፡

ደራሲ አውገቸው ተረፈ “ማሞ ቢጩ” በተሰኘ ሥራው የሱስን አደገኛነት ለትውልድ አበክሮ አስተምሯል፡፡በዚህ ድርሰት መጠጥን ጨምሮ ማንኛውም ሱስ አምጭ ነገሮች በደስታ ተጀምረው ልንወጣው የማንችለው አዙሪት ውስጥ ሊከቱን እንደሚችሉ እያዋዛ አስተምሮናል፡፡

አውግቸው ከአልፎ አልፎ ከሚነሳበት ህመሙ በስተቀር ከሰዎች ጋር ተግባብቶ የሚያስኖር ጥሩ ጠባይ ነበረው ይባላል፡፡ባሴ ሐብቴ ከሚባል የጎጃም ተወላጅ እና ድንቅ ደራሲ ጋር ለረዥም ዓመታት በደባልነት አብረው ኖረዋል፡፡ ባሴ ሐብቴ ማለት የጋዜጠኛ እና ደራሲ ስንዱ አበበ የአንድ ዘመን የፍቅር ጓደኛ ነበር፡፡ አሁን በሕይወት የለም፡፡ነፍስ ይማር!!

በኢትዮጵያ በየዓመቱ የሚካኼደው 4ተኛው የበጎ ሰው ሽልማት ነሐሴ 28 ቀን 2008 ዓ/ም በአቤል ሲኒማ ተከናውኗል፡፡ በዕለቱ ደራሲ አውግቸው ተረፈ በሥነ ፅሑፍ ዘርፍ ለአገርና ለህዝብ ላበረከተው ታላቅ አስተዋፅኦ በኪነ ጥበብ (ድርሰት) ዘርፍ የ2008 ዓ.ም የበጎ ሰው ሽልማት አሸናፊ ሆኖ ሽልማቱን ከደራሲ አያልነህ ሙላቱ እጅ ተቀብሏል፡፡ መሸለሙ ተገቢ ነው፡፡ ደራሲ ዶክተር እንዳለጌታ ከበደ አውግቸው ተረፈን “ፅፈነው የማያልቅብን አውግተነው የሚተርፍብን አይነት ሰው ነው” ሲል ይገልፀዋል፡፡

የደራሲ አውግቸው ተረፈ የትዳር እና የቤተሰብ ሁኔታ በተመለከተ በ1969 ዓ/ም ጎጃም ቤተሰብ ጥየቃ እንደኼደ ቤተሰቦቹ የመጀመሪያው የሆነችውን ሚስቱን ዳሩት፡፡ትዳራቸው ለአመት ብቻ ነበር የዘለቀው፡፡በኋላ በ1987 ዓ/ም ሁለተኛ ሚስቱን አገባ፡፡ልጆችንም ወለደ፡፡አውግቸው የጋራ መኖሪያ ቤት (ኮንዶሚኒዬም) ቤት ደርሶት ቃሊቲ ገላን ኮንዶሚኒየም ሲኖር ቆይቶ ሞት የሰው ልጅ ሁሉ የማይቀር ዕዳ በመሆኑ ያ ታላቅ የኪነ ጥበብ ሰው ሰኔ 10/2011 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ፡፡